የኢትዮጵያ
ኢንተርፕራይዝ ልማት

# የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማትን አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 526/2015


**Address**

https://t.me/ethiopianenterprisedevelopment

ethiopianenterprisedevelopment

@ethiopianenterprisedevelopment

https://www.sme.gov.et/

ethiopianenterprise@gmail.com

+25115511122 /+251115150333


በኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

በኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

# Telegram

ስካን ያድርጉት

# Facebook

ስካን ያድርጉት

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ባለፉት 80 ዓመታት አምራችነትን በሐገራችን በማስተዋወቅና በማስፋት፣ ለአነስተኛ አምራቾች ምቹና ተመራጭ የሆኑ ሙያና ክህሎቶችን በማስጨበጥ፣ ቴክኖሎጂ በማስታጠቅና ዜጎች አስተማማኝ ገቢ እንዲኖራቸው ለማስቻል ጥረት ሲያደርግ የነበረ ታሪካዊ ተቋም ነው፡፡

ተቋሙ በተለያዩ ወቅቶች ልዩ ልዩ የተልዕኮ ማሻሻያዎችን በማድረግ ከጥቃቅን ቢዝነሶች ድጋፍና ስራ ዕድል ፈጠራ ጀምሮ የነበረውን ተልዕኮ እያሻሻለ፣ አዳዲስ ተቋማትንም ከውስጡ እያዋለደ ይበልጥ ለአምራች ዘርፉ ትኩረት እየሠጠ እንዲሄድ ተደርጓል፡፡

በዚህም መነሻነት ተቋሙ ትኩረቱን በአምራች አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ላይ በማድረግ ዘርፉ ተወዳዳሪ ሆኖ በኢኮኖሚያዊ ሽግግር፣ በተኪ ምርት ልማት፣ በስራ ዕድል ፈጠራና ኤክስፖርት እድገት ላይ የራሱን ጉልህ ሚና እንዲጫወት ለማድረግ በ2015 ዓ.ም በአዲስ መልክ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

ይህ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ቁጥር 526/2015 የፀደቀ አዲስ ማቋቋሚያ አዋጅ ተቋሙ በተሟላ ሁኔታ የአምራች ኢንተርፕራይዝ ዘርፉን ለመደገፍና እንደሐገር ያሉ አቅሞችን አሠባስቦ ለመምራት የሚያስችለው ነው፡፡ በመሆኑም በአዲሱ ደንብ መሠረት ተቋሙ ለአነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች ችግር ፈቺ የአቅም ግንባታ ስራዎችን፣ የፋይናንስና የማምረቻ መሳሪያ አቅርቦትን፣ የቴክኖሎጂና የምክር አገልግሎቶችን፣ የማምረቻ ቦታና መሰረተ-ልማት ግንባታና አስተዳደር ስራዎችን፣ የግብዓትና የገበያ ትስስር ድጋፎችንና መሠል ድጋፎችን በመስጠት ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የማስፋፋትና የማሸጋገር ተልዕኮ ያለው ተቋም ወደ መሆን ተሸጋግሯል፡፡

ይህ ሠነድም የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የተቋቋመበትን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 526/2015 የያዛቸውን አንኳር ጉዳዮች በተሟላ ሁኔታ ለማስተዋወቅ የተዘጋጀ ነው፡፡



# የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማትን አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 49(2) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ ደንብ ቁጥር 526/ 2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃል አገባቡ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1/ ''ኢንተርፕራይዝ'' ማለት ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ነው፤

2/ ''ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ'' ማለት ማሽንን፣ መሣሪያን ወይም የሰው ኃይልን በመጠቀም ጥሬ ዕቃ ላይ የቅርጽ፣ የመጠን ወይም የይዘት ለውጥ በማድረግ የተሻለ ዋጋ ያለው ምርት የሚያመርት ነው፤

3/ "ጥቃቅን ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ" ማለት እስከ 10 (አስር) ቋሚ ሰራተኞች የያዘ እና እስከ ብር 600,000 (ስድስት መቶ ሺህ) ጠቅላላ ሐብት ያለው ኢንተርፕራይዝ ነው፤ ሆኖም ግን በሰው ኃይልና በጠቅላላ ሐብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሐብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤

4/ **"አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት ከ 11 (አስራ አንድ) እስከ 50 (ሃምሳ) ቋሚ ሰራተኞች የያዘ እና ከብር 600,001 (ስድስት መቶ ሺህ አንድ) እስከ ብር 10,000,000 (አስር ሚሊዮን) ጠቅላላ ሐብት ያለው ኢንተርፕራይዝ ነው፤ ሆኖም ግን በሰው ኃይልና በጠቅላላ ሐብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሐብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤

5/ **"መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት ከ 51 (ሃምሳ አንድ) እስከ 100 (መቶ) ቋሚ ሰራተኞች የያዘ እና ከብር 10,000,001 (አስር ሚሊዮን አንድ) እስከ 90,000,000 (ዘጠና ሚሊዮን) ጠቅላላ ሐብት ያለው ኢንተርፕራይዝ ነው፤ ሆኖም ግን በሰው ኃይልና በጠቅላላ ሐብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሐብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤

6/ **"ከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት ከ100 (መቶ) በላይ ቋሚ ሰራተኞች የያዘ እና ከብር 90,000,000 (ዘጠና ሚሊዮን) በላይ ጠቅላላ ሐብት ያለው ኢንተርፕራይዝ ነው፤ ሆኖም ግን በሰው ኃይልና በጠቅላላ ሐብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሐብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤

7/ **''የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት''** ማለት የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ችግር የለየና በፍላጐት ላይ የተመሠረተ የተሟላ መረጃ የማደራጀትና የመስጠት፣ ስልጠናና ምክር፣ ቴክኖሎጂ ልማት፣ ግብይት፣ የጥራትና ምርታማነት ማሻሻያና ሌሎች መሰል ድጋፎችን መስጠትን እንዲሁም በተለያዩ ተቋማት የሚሠጡ አስፈላጊ ድጋፎችን ማመቻቸትን የሚያካትት ድጋፍ ነው፤

8/ "የዘርፍ ማኅበር" ማለት አምራች ድርጅቶች በየተሰማሩበት መስክ የጋራ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ያቋቋሙት ህጋዊ ማኅበር ነው፤

9/ ''ሚኒስቴር'' ማለት ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፤

10/ "ልማት" ማለት የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ማለት ነው፤

11/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 47 መሰረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬዳዋ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

12/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. ዋና መስሪያ ቤት

የልማቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

## 4. ዓላማ

*ልማቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-*

1/ ኢንተርፕራይዞች እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ በማድረግ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍልን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት መደገፍ፣ ለከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት መሠረት መጣል፤

2/ ኢንተርፕራይዞችን ለማስፋፋትና ለማጠናከር አስፈላጊ መሰረተ-ልማቶችን በማልማትና በማስተዳደር ዘርፉን ተወዳዳሪና ውጤታማ እንዲሆን ማስቻል፡፡

## 5. የልማቱ ስልጣንና ተግባር

*ልማቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-*

1/ የኢንተርፕራዝ ልማትንና ሽግግርን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ፕሮግራምና ፕሮጀክቶች እንዲወጡ ሐሳብ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ተዘጋጅቶ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2/ የኢንተርፕራይዝ ልማቱን የሚደግፉ የድጋፍ ማዕቀፎችን፣ የአሰራር ስርዓቶችን እና እቅዶችን ያዘጋጃል፤ ይተገብራል፤ ተግባራዊ እንዲሆኑም ያስተባብራል፤

3/ ለኢንተርፕራይዞች በተለይም ገቢ ምርቶችን ለሚተኩ እና ምርታቸውን ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ኢንተርፕራይዞች ተወዳዳሪነትና ውጤታማነት ማነቆ የሆኑ ጉዳዮች በጥናት እንዲለዩና መፍትሄ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

4/ ዜጎች በኢንተርፕራይዝ ልማት እንዲሰማሩ የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ሥራ ይሠራል፣ የራሳቸውን ኢንተርፕራይዝ አቋቁመው ወደ ስራ እንዲገቡ ከሚመለከታው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

5/ የኢንተርፕራይዝ ልማቱን የሚደግፉና የሚያስተባብሩ የክልል ተቋማትን፣ የባለድርሻ አካላትን፣ የልማቱን ሰራተኞችና የዘርፍ ማኅበራትን የማስፈፀም አቅም ይገነባል፤የአቅም ግንባታ ስራ ከሚሰሩ ሌሎች ተቋማት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

6/ ለኢንተርፕራይዞች አስፈላጊ የሆኑ የስልጠና፣ የጥናት፣ የፋይናስ፣ የማምረቻ መሳሪያ፣ የቴክኖሎጂ፣ የምክር አገልግሎት፣ የማምረቻ ቦታና መሰረተ-ልማት፣ የግብዓት፣ የገበያ ትስስርና ሌሎች ድጋፎች በክፍተትና በዕድገት ደረጃ ላይ ተመስርተው እንዲቀርቡ ያደርጋል፤ ይደግፋል፣ ያስተባብራል፤

7/ ከሚኒስቴሩ ጋር በመተባበር የኢንተርፕራይዞችን ልማትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችል የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ይሠጣል፣ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ያስተባብራል፤



8/ የኢንተርፕራይዝ ልማትን ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር ይለያል፣ ይቀምራል፣ እንዲሰፋ ያደርጋል፤

9/ ለኢንተርፕራይዞች ጠቃሚ የሆኑ ፕሮጀክት ፕሮፋይሎች፣ ሞዴል ቢዝነስ ፕላኖችና ስፔሲፊኬሽኖች ያዘጋጃል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

10/ በልማቱ ስር የሚገኙ መሰረተ ልማቶችን በመጠቀም ለኢንተርፕራይዞች እና በዘርፉ መሰማራት ለሚፈልጉ ዜጎች ስልጠና ይሠጣል፣ እንዲሠጥ ያደርጋል፣ መለዋወጫዎችንና ችግር ፈች የሆኑ የምርትና የቴክኖሎጂ ናሙናዎችን ያዘጋጃል፣ በስልጠና ያሸጋግራል፤ የፈጠራ ሃሳብ ይዘው ለሚመጡ ዜጎች ሃሳባቸውን ወደ ተጨባጭ ምርት እንዲለውጡ ያደርጋል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

11/ የኢንተርፕራይዞች የቁጠባ ባህል እንዲያድግና የስራ ማስኬጃና የማምረቻ መሳሪያ ፋይናንስ ከአበዳሪና ከአከራይ ተቋማት እንዲያገኙ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ምቹ የፋይናንስ አቅርቦት ስርዓት ይዘረጋል፤

12/ ለኢንተርፕራይዝ አገልግሎት የሚውሉ መሰረተ-ልማት የተሟላላቸው የማምረቻ፣ ማሳያና መሸጫ ማዕከላት ያለማል፣ ያስተዳድራል፤

13/ ኢንተርፕራይዞች እርስ በእርስና ከከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች፣ ከሌሎች ተቋማትና ድርጅቶች ጋር በግብዓት፣ በገበያና በቴክኖሎጂ የሚተሳሰሩበትን ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

14/ ኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ወርሃዊ፣ ክልላዊ፣ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ አውደ-ርዕይ ያዘጋጃል፤ ክልሎች እና የግል ተቋማት በተናጠልና በጋራ እንዲያዘጋጁ ያመቻቻል፣ በአገር ውስጥና በውጭ አገር በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽኖች ላይ ኢንተርፕራይዞች እንዲሳተፉ ያደርጋል፤ይደግፋል፤

15/ ኢንተርፕራይዞችን ተወዳዳሪ ለማድረግና ዜጎች ወደ ዘርፉ እንዲገቡ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በጥናት ላይ የተመሠረተ የማበረታቻ ስርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከተው አካል ጋር በጋራ ይሰራል፤ ተፈጻሚነቱን ያረጋግጣል፤

16/ ለኢንተርፕራይዞች የአንድ መስኮት አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላት እንዲቋቋሙና ወደ ስራ እንዲገቡ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር ይሰራል፤




17/ በኢንተርፕራይዝ የሚመረቱና ጥራታቸውን የጠበቁ ምርቶች ደረጃ እንዲወጣላቸውና የወጣላቸውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

18/ ኢንተርፕራይዞችን ለመደገፍ ተመሳሳይ አላማ ካላቸው በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር የትብብር ስምምነት ያደርጋል፣ ተፈጻሚ እንዲሆንም ይሰራል፤

19/ ለዘርፉ ልማት አጋዥ የሆኑ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂዎች እንዲለሙ ያደርጋል፤ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ መረጃዎችን ያደራጃል፣ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤

20/ ኢንተርፕራይዞች በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ድጋፍ ያደርጋል፣ ይከታተላል፤

21/ ልማቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ መሰረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ክፍያ ያስከፍላል፤

22/ የጥቃቅን ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ልማትና ሽግግር በተመለከተ ከስራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የድጋፍ ስራ ይሠራል፣ አስፈላጊውን አሰራሮች ይዘረጋል፤

23/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ ውል ይዋዋላል፤ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

24/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 6. የልማቱ አቋም

**ልማቱ፡-**

1/ በመንግስት የተሾመ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና

2/ አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡



## 7. የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር

1/ ዋና ዳይሬክተሩ የልማቱ ዋና ስራ አስፈጻሚ በመሆን የልማቱን ስራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 የተመለከቱትን የልማቱን ስልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ህጐች መሰረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የልማቱን ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅዶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ይተገብራል፤ የአፈጻጸም ሪፖርትም ያቀርባል፤

መ) የልማቱን በጀት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ በተፈቀደው በጀትና የስራ ኘሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ልማቱን ይወክላል፤

ረ) የልማቱን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፡፡

3/ ለልማቱ ስራ ቅልጥፍና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለልማቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ወይም ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 8. የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ስልጣንና ተግባር

*ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፡-*

1/ የዘርፋቸውን ተግባር በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበርዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፤

2/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጣቸውን ስራዎች ያከናውናሉ፤

3/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዋና ዳይሬክተሩን ወክሎ ይሰራል፡፡

## 9. በጀት

***የልማቱ በጀት በመንግስት ይመደባል፡፡***

## 10. ስለ ሂሳብ መዛግብት

**1/ ልማቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤**

**2/ የልማቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡**

## 11. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

***ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡***

***አዲስ አበባ ሕዳር 19 ቀን 2015 ዓ.ም***

***ዐቢይ አህመድ አሊ(ዶ/ር)***
***የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ***
***ጠቅላይ ሚኒስትር***